# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

13

★ አዲስ ምዕራፍ

★ የዓለም ሕዝቦች አብዮታችንን ይደግፋሉ

★ የሶሻል ዲሞክራሲ ሁለት ታክቲኮች

★ የካፒታሊስት ሥርዓተ ማኅበር

ጥቅምት ፴ — ፲፱፻፷፱ ዓ. ም.

## ርእሰ አንቀጽ ።

# አዲስ ምዕራፍ

ኢምፔሪያሊዝም የመላ የዓለም ሕዝቦች ጠላት ነው ። በአንድ ሀገር ክልል ውስጥ የሚገኙ በዝባዦችና ጨቋኞች ኩታ ገጠም ከሆኑ ሌሎች በዝባዦችና ጨቋኞች ጋር የጠበቀ የመደብ አንድነትና ትብብር አላቸው ። ከዚህም አልፈው በዓለም አቀፍ ደረጃ ወንዞችን ፤ ውቅያኖሶችን ፤ ተራሮችን እያቋራረጠ የሚያስተሣሥራቸው የመደብ ጥቅም አላቸው ። በተበዝባዦችም በኩል ደግሞ እንደዚሁ ነው ። በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሣሠሩ ጨቋኝ ኃይሎችን ተበዝባዦችና ጭቁን ሕዝቦች ሊቋቋሙና ሊደመስሱ የሚበቁት እነሱም በዓለም አቀፍ ደረጃ የመደብ አንድነታቸውን ማጠንከር ሲችሉ ነው ። የዓለም ጭቁን ሕዝቦች ትግል ጠረፍ ፤ ቀለም ዘር ፤ ቋንቋን ሁሉ አቋርርጦ የመላ ዓለም በዝባዥና ጨቋኝ ኃይሎችንና አስተባባሪያቸውን ኢምፔሪያሊዝምን ለመደምሰስ የሚሆነውና መሆንም ያለበት ለዚህ ነው ።

ኢምፔሪያሊዝም የጠቅላላው የመላ ዓለም በዝባዥ ጨቋኝ ኃይሎች ቀንደኛ መሪና አስተባባሪ በመሆኑ ፤ የመላ ዓለም ተበዝባዦች ቀንደኛ ጠላት ነው ። ዛሬ በዓለም ላይ ያለ ማንም ሕዝብ ለነፃቱ ፤ ለብሔራዊ ካብሩና መብቱ የሚያደርገው ትግል ከዚህ የዓለም ሕዝቦች የጋራ ጠላት ከሆነው ከኢምፔሪያሊዝምም ጋር መሆን ያለበትም ለዚህ ነው ። አንድ ሕዝብ ለነፃነቱ ሲታገል በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ ካላደረገና ኢምፔሪያሊዝም እንዲደክም ፤ እንዲደመሰስ ድርሻውን ካላበረከተ በምንም ዓይነት ዋስትና ያለው ነፃነት ሊኖረው አይችልም ።

ስለሆነም ዛሬ በየትኛውም ክፍለ ዓለም ጭቁን ሕዝቦች ለነፃነታቸው የሚያደርጉት ተጋድሎ የጠቅላላው ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል የማይነጠል አካል ነው ። በየትም ይሁን በየት ጭቁን ሕዝቦች በኢምፔሪያሊዝም ላይ የሚጐናጸፉት ድል የራሳቸው ብቻ ሳይሆን በመላ ዓለም ጭቁኖች የጋራ ጠላት ላይ የተገኘ ድል ነው ። ስለሆነም በዛሬዪቱ ዓለም በየትኛውም ክፍል የሚደረግ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ድል ድላችን እንደመሆኑ መጠን ፤ የማንም ጭቁን ሕዝብ ትግል ትግላችን ነው ። በዚሁ አንጻር የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች በትግላቸው የሚጐናጸፏቸው ድሎች የመላ ዓለም ተራማጆች ድሎች ናቸው ። ትግላቸውም የመላ ዓለም ሕዝቦች ትግል አካል ነው ።

አብዮታችን እየገፋ በሔደ ቊጥር በአገር ደረጃ ብቻ ሳይሆን የጭቁን ሕዝቦች ትግል በዓለም አቀፍ ደረጃ ወዳጅና ጠላቶችን እየለየ መሔዱ የማይታበል ሀቅ ነው ። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የአብዮታዊ ትግላችን ዓለም አቀፋዊ መልክ ጐልቶ የሚታይበት ሁኔታ አልነበረም ። አብዮቱ እየገፋ ሲሔድ ግን ፀረ ኢምፔሪያሊስት ይዘቱ እየጠራ በመሔዱ ጭቁን የዓለም ሕዝቦች ከመቸውም ይበልጥ ትግላችንን እንደትግላቸው ቆጠሩት ። የኢትዮጵያ ጭቁኖችም ከመቸውም ይበልጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሰው ልጅ መብት ነፃነትና እኩልነት የሚደረገውን ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል የራሳቸው አድርገው ከዓለም ጭቁኖች ጐን መሰለፋቸውን በይፋ የሚያረጋግጡበት ከፍተኛ የትግል ደረጃ ላይ ደረሱ ።

በሀገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ጭቁን ኢትዮጵያውያን እጅግ በጋለ ስሜት ከዳር እስከዳር ተነሣሥተው ያከበሩት « የደቡብ አፍሪካ ታጋዮች የድጋፍ ሳምንት » ና በዚህ የድጋፍ ሳምንት መጨረሻ ላይ ከጥቅምት ፳ እስከ ፳፫ ድረስ ለደቡብ አፍሪካ ሕዝቦች ድጋፍ ለመስጠት የተደረገው የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ አስቸኳይ ጉባኤ የኢትዮጵያ ጭቁኖች ትግላቸውን በይፋ ወደዓለም አቀፍ መድረክ ያሸጋገሩበት አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ድርጊት የሚሆነው ለዚህ ነው ።



የዚህ የመጀመሪያው ዓለም አቀፍ አስቸኳይ ጉባኤ የተዘጋጀው በአፍሮ ኤሽያ ሕዝቦች የአንድነት ድርጅትና በደቡብ አፍሪካው «የአፍሪካውያን ብሔራዊ ሸንጎ» በተባለው ታጋይ ድርጅት ትብብር ነው ። በዚህ ጉባኤ ላይ ከ፺፫ አገሮች የመጡ የመላ ዓለም ታጋይ ሕዝቦችን የሚወክሉ ፩፻፰ የሚሆኑ የመንግሥታት ፤ የተራማጅ ድርጅቶች ፤ የብሔራዊ ነፃ አውጪ ንቅናቄዎች ወኪሎች ተገኝተው ነበር ።

በዚህ ጉባኤ ላይ የዓለም ተራማጅ ኃይሎች ለደቡብ አፍሪካ ታጋዮች በተቀነባበረ መልክ መስጠት ስላለበት የፖለቲካና የማቴሪያል ድጋፍ ተወያይተው ጠቃሚ የሆኑ ውሳኔዎችን አሳልፈዋል።

በዚህ ጉባኤ ላይ ተሳታፊዎቹ ለኢትዮጵያ አብዮት ያላቸውን ድጋፍ በመግለጽ በዚሁ መጽሔታችን ያቀረብነውን አብዮታዊ መልእክት ለኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት አስተላልፈዋል ።

በጉባኤው መጨረሻ ላይ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ከደቡብ አፍሪካ ታጋይ ሕዝቦች ጋር ብቻ ሳይሆን ከመላ ዓለም ተራማጆች ጋር ያላቸውን የትግል አንድነት ለመግለጽ የአዲስ አበባ ኗሪዎች በአብዮት ዓደባባይ እጅግ ደማቅ የሆነ ሕዝባዊ ስብሰባ አድርገዋል ። በዚህ ስብሰባ ላይ የአዲስ አበባ ኗሪ ሕዝብ በልዩ ልዩ አብዮታዊ መዝሙሮችና መፈክሮች ድጋፉን ከማሰማቱም በላይ ፤ ከልዩ ልዩ አገሮችና ድርጅቶች የተወከሉ አብዮታውያን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ያላቸውን አንድነት በመግለጽ ለሕዝቡ ንግግሮች አድርገዋል ።

ሰሞኑን እንደተገነዘብነው የዚህ ጉባኤ አዲስ አበባ ላይ መደረግ የዓለም ተራማጅ ሕዝቦች በአብዮት ትግል አፍላ ውስጥ ለምትገኘው አገራችን ሆን ብለው የሰነዘሩት የድጋፍ ድርጊት ነው ። የኢትዮጵያ አብዮት የዓለም ሕዝቦችን ድጋፍ በሰፊው እንዳገኘ ሁሉ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብም በመላ ዓለም የሚደረገውን የነፃነት ተጋድሎ እንደራሱ ትግል ቆጥሮ በሙሉ ልብ መደገፉን በመላ ኢትዮጵያ ሰሞኑን የታየው የድጋፍ እንቅስቃሴ በገሐድ አሳይቷል ።

በዚህም አብዮታችን በዓለም ተራማጆች በይፋ የታቀፈበት እሱም መልሶ የዓለም ጭቁኖችን ትግል እንደራሱ ትግል አድርጐ ያቀፈበት አዲስ የድል ምዕራፍ ተቀዳጅቷል ።

እስከዛሬ ድረስ አብዮታችንን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማጥላላት ፤ የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝብ ከተቀሩት ታጋይ የዓለም ሕዝቦች ለመነጠል ሲደረግ የነበረው የተቀነባበረ የኢ. ሕ. አ. ፓ. ኢ.ዲ.ዩና የኢምፔሪያሊስቶች ሴራ እየከሸፈ መሔዱ ፤ እነዚህ ፀረ አብዮት ኃይሎች በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የተተፉትን ያህል የዓለም ተራማጆችም እየነቁባቸው እንደሔዱ ከእንግዲህ ማንም ሊጠራጠር አይችልም ።

ነገር ግን እነዚህ ፀረ አብዮት ኃይሎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዓለም ጭቁኖች ጐን እንዳይሰለፍ ፤ የዓለም ጭቁኖች ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጐን እንዳይቆሙ የሚያደርጉትን መፍጨርጨርና የሚያካሂዱትን ፀረ ኢትዮጵያ አብዮት ፕሮፓጋንዳ መቀጠላቸው አይቀርም ። ነገር ግን የኢትዮጵያ አብዮት በየጊዜው የሚጋረጥበትን መሰናክል ሁሉ እያሸነፈ ወደፊት መገስገሱ የማይቀር የታሪክ ሐቅ ነውና በዓለም አቀፍ ደረጃ ፀረ አብዮት ኃይሎች የሚነዙበትን ፕሮፓጋንዳ አክሽፎ ከዓለም ጭቁኖች ጋር ከብረት የጠነከረ አብዮታዊ አንድነቱን እንደሚመሠርት ምንም ጥርጣሬ የለንም ። ሰሞኑን በኢትዮጵያ የታየው ከፍተኛ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ፤ የዓለም ተራማጆች በአዲስ አበባ ያደረጉት ለደቡብ አፍሪካ ሕዝቦች የድጋፍ ጉባኤ ፤ የተከተሉት ውሳኔዎችና በአዲስ አበባ አብዮት ዓደባባይ የተደረገው እጅግ ደማቅ የሆነ ስብሰባ የኢትዮጵያ ጭቁኖች ከዓለም ጭቁኖች ጋር ትግላቸውን ለማዋሐድ በሚያደርጉት የትግል ጉዞ ላይ እንደ አንድ ታላቅና አዲስ ምዕራፍ የሚቆጠር አብዮታዊ ድል ነው ።

የዓለም ሕዝቦች አንድነት ለዘለዓለም ይኑር
ኢምፔሪያሊስቶችና ቡችሎቻቸው ይውደሙ !
አብዮታዊት ኢትዮጵያ ።